ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
የእቴጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
በ2014 ዓ.ም ክልላዊ ፈተና በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች ለወሰዳችሁ ሴት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ

የእቴጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ቀጥሎ የተቀመጠውን የቅበላ መስፈርት የሚያሟሉ ሴት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን አወዳድሮ ለመቀበል ዝግጅት ያደረገ ሲሆን መስፈርቱን የምታሟሉ ሴት ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ በመምጣት መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

1. **ለ9ኛ ክፍል ለሚወዳደሩ ሴት ተማሪዎች**

   1.1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ባሉት **የመንግስትና የግል ትምህርት** ቤቶች በ2014 ዓ.ም ተማሪ በመሆን ያጠናቀቁ

   1.2. በትምህርት ቤት ቆይታቸው ወቅት መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው ስለሆነ ከተማሩበት ትምህርት ቤት ማረጋገጫ ደብዳቤ የሚያቀርቡ

   1.3. በትምህርት ቤት ውስጥ በተቋቋሙት ተጓዳኝ ክበባት ቢያንስ በአንዱ ጉልህ ተሳትፎ ማድረጋቸውን የማረጋገጫ ደብዳቤ የሚያቀርቡ

   1.4. የመግቢያ ፈተና ለመፈተን ፍቃደኛ የሆኑና የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት የቻሉች

   1.5. ለአዳሪ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በወጣው ህግና ደንብ መሰረት ለመማር ፍቃደኛ የሆነች

   1.6. የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል አማካኝ የክፍል ውጤት 75% እና በላይ ያስመዘገቡና በጽሑፍ ይዞ የሚቀርቡ

   1.7. በ2014 ዓ.ም በስምተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና የጥሬ ማርክ ውጤታቸው 75% እና በላይ የሆነ እና በትምህርት ቤቱ ማህተም የተረጋገጠ ደብዳቤ ይዞ መቅረብ የሚችል